# ደምጸ — ደብተራው

ከአለቱ

ነበር እምነታችን፣ ቃል ኪዳን ላናፈርስ፣
ነበር ዓላማችን፣ የግፍ እንባ ማበስ፣
ተዋውለን ነበር፣ ቃላባይ እንዳንሆን፣
እንዳንከዳዳ፣
ቢመር ቢጎመዝዝ፣ ቢኾርጎደጉድብን፣
የመከራ ናዳ።

ውልም ተፈጣጥመን፣ በደም የቀለመ፣
ባጥንት የተማሰ፣ በነብስ የታተመ፣
ተማምለን ነበር፣ ላንዴም ለሁልዬም፣ እንዳንከዳዳ፣
እንዳንሆን ተወቃሽ፣ የታሪክ ባለዳ፣
ልንኖር ጸድተን፣ ከህሊና ዕዳ።

በሰው መሰል ፍጡር፣ ሕይወት ለገበሩ፣
በተራራው ስር፣ እሳር በቅሎባቸው፣
በስብሰው ለቀሩ፣
ስጋቸውን ለምስጥ፣ አጽማቸውን ለጅብ፣
ለመስጠት ላልሳሱ፣
እንደወራጅ ውሃ፣ የሕይወትን ጅረት፣ ደምን ላፈሰሱ፣
ተማምለን ነበር፣ ለመተኪያ አልቦቹ፣ ልንሆን ባለአደራ፣
በከፈሉት ግብር፣ መከራ ሊያባራ፣
ልንቀጥል ትግሉን፣ አሽቶ እስከሚያፈራ።
ነበረ ሲጀመር፣ የነንዶች ትግሉ፣
የማታ የማታ፣ የሁዋላ የሁዋላ፣
እንደሰራ አይገድል፣ ሆኖም ቢገኝ ቅሉ!!!